ሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት

ከምክር ቤት ፕሬዚደንት ሮጀር በርሊነር ቢሮ ሜይ 18, 2017

አድራሻ፣ ኒል ኤች ግሪንበርገር 240-777-7939 / ደሊፋይን ሃሪሰን 240-777-7931
ሶኛ ሂሊይ 240-777-7926 / ናሚታ ኦርካርያ 240-777-7819

የ ዜ ና ስ ር ጫ ት

በFY18 የስራ በጀት ስምምነት እና በFY17-22 ካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም ላይ የሞንትጎመሪ ምክር ቤት ፕሬዚደንት በርሊነር የሰጡት አስተያየት

ሮክቪል፣ ኤምዲ፣ ሜይ 18, 2017—ሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት ፕሬዝደንት ሮጀር በርሊነር በዛሬው እለት ምክር ቤቱ የሙሉ ድምጽ ስምምነቱን በካውንቲው 2018 የበጀት አመት የስራ በጀት ስምምነት እና በ2017-22 የበጀት አመቶች ካፒታል ማሻሻያዎች ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል። በጀቱ በምክር ቤቱ በስርዓት የሚጸድቀው በሜይ 25 ነው።

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት በርሊነር አስተያየት ሙሉ ጽሁፍ፣

ባልደረቦች እና የካውንቲው ነዋሪዎች፣

በጀቶች ብዙ ነገሮች ናቸው። እሴቶቻችንን፣ ለዋና ዋና የመንግስት አገልግሎቶች ያለንን ቁርጠኝነት፣ እንዲሁም የካውንቲያችንን እና የነዋሪዎቻችንን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ያንጸባርቃሉ። ያጸደቅነው በጀት እውነተኛውን የፊዚካል ሁኔታችንን ከእሴቶቻችን ጋር ሲያጣጥም ነዋሪዎቻችንን እና ግብር ከፋዮቻችን በየቀኑ የሚያዩት እና የሚተማመኑበትን መሰረታዊ አገልግሎቶች ላይ የተመሰረተ እንደሆነ አምናለሁ።

የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ ለብዙ አመታት እንዳደረጉት አስተማማኝ ብሉፕሪንት አቅርበውልናል። በጀታችን በመሰረታዊዎቹ ላይ ተመስርቶ በአንገብጋቢ ፍላጎቶች ላይ መሻሻልን ያደርጋል። በተመሳሳይ ወቅት፣ በጀታችን በንብረት ግብሮች ላይ ያለውን መስመር ጠብቆ የፊዚካል ሃላፊነት ባህልን በማስቀጠል የኢኮኖሚያዊ ማእበሎችን የምንቋቋምበት እና በጥሩ ሁኔታ የሚተዳደሩ መንግስቶች መገለጫ የሆነውን የተከበረውን ኤኤኤ ቦንድ ደረጃንን እንድናስጠብቅ አስችሎናል። ፊዝካል እቅዳችንን ለማስከበር ተወዳዳሪ የሌለውን $457 ሚሊዬን የተመደበ ሲሆን፣ የ 8.9 በመቶ መጠባበቂያም ያስፈልገዋል። ይህ በጀት መንግስታችን በየቀኑ እንዲንቀሳቀስ ብዙ የሚያደርጉትን የካውንቲውን ሰራተኞቻችንንም ይደግፋል።

እንደሁልጊዜም፣ የካውንቲያችን ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጣቸው እና በጣሙን መሰረታዊ ሃላፊነቶች አንዱ ትምህርት ነው። የትምህርት ቤት ሲስተማችንን $2.5 ቢሊየን በጀት ጥያቄ 100 በመቶ ስንደጉም፣ ይህም የክፍል መጠንን ለመቀነስ እና የትምህርት ውጤታማነት ክፍተትን ለመሙላት የምናደርገውን መሻሻል ለማስቀጠል ይጠቅመናል። በካውንስሉ፣ በትምህርት ቦርዱ፣ ሱፐርኢንቴንደንት ስሚዝ እና በትምህርት

ስርዓቱ መሃከል ያለው ትብብር የሚያንጸባርቀው አለም አቀፋዊ ደረጃ ያለውን ትምህርት ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ለማቅረብ ያለንን የጋራ ቁርጠኝነትን እንዲሁም መሻሻላችንን ለመለካት የሚያስችለንን ግልጽነት የተሞላበት መለኪያችንን እንደምንጠቀም ነው። ከኤምሲፒኤስ ባልደረቦቻችን ጋር በእውነተኛ አጋርነት መስራታችን እያደገ የመጣውን የትምህርት ቤት ስርዓታችንን ጽኑ ፍላጎቶች እንድናሙዋላ እና በአገሪቱ ካሉ እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት ስርዓቶች አንዱ ሆኖ እንዲቀጥል ማረጋገጥ ነው።

በተጨማሪም በካፒታል ማሻሻያ በጀት የትምህርት ቤት ስርአቱን ጥያቄ 100 በመቶ ደጉመናል። ስርአታችን በየአመቱ ከ 2,000 እስከ 3,000 ተማሪዎች ማደጉን ሲቀጥል፣ ትምህርት ቤቶቻችን ጫናውን እየተሰማቸው ነው። ካውንስሉ ተማሪዎቻችን እና አስተማሪዎቻችን ለመማር ማስተማር አመቺ የሆነ ሁኔታ እንዲኖር የትምህርት ስርአቱን ንብረቶች ለመደጎም ያለውን ቁርጠኝነት መግለጹን ይቀጥላል።

ትምህርትን በተመለከተ፣ ልጆቻችን በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሳካላቸው ለማረጋገጥ ከሚያስችሉት ወጭ ቆጣቢ ዘዴዎች አንዱ በቅድመ ትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ነው። እንደ ኒው ዮርክ፣ ፊላደልፊያ፣ እና ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የመሳሰሉት ማህበረሰቦች ይህንን በትልቅ መንገድ እየተገበሩት ነው። ይህን የመሰለ ላቅ ያለ መንገድ ለመጀመር ተጨማሪ ስራ ማከናወን ይኖርብናል፤ ነገር ግን በዛው አቅጣጫ የሚያስኬደን ትናንሽ እርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን፤ እየወሰድንም ነው። ለቅድመ መዋለ ህጻናት እና ከዝቅተኛ ገቢ ቤተሰቦች የመጡ ተማሪዎችን የሚያገለግሉ ሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ከ $4.5 ሚሊዮን በላይ በዚህ በጀት ውስጥ ጨምረናል።

በጀታችን በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ኮሌጅን እየጨመረ የመጣውን አስፈላጊነት ያመለክታል። ከካውንቲያችን ታላላቅ ሃብቶች እና አስተካካዮች አንዱ ሲሆን፣ የሚያገለግለውም በሁሉም እድሜዎች፣ የኑሮ ሂደቶች ያለፉ እና ዘሮችን የሚያካትት ከ 60,000 በላይ ተማሪዎችን ነው። የካውንቲያችን ታላቅ መስታወት ሲሆን፣ እኛም ፍላጎቱን ለማሳካት ጠንክረን በመስራት ተጽእኖውን ለማጠናከር እና የሚያቀርበውን ጥራት ያለው ፕሮግራሚንግ ለመደገፍ የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ ካመለከተው በ $3.2 ሚሊዮን የሚበልጥ አቅርበንለታል።

በካውንቲው ስራ ማስፈጸሚያ በጀት ላይ ካደረግናቸው ትልቅ ለውጦች አንዱ እርዳታ በጅጉን የሚያስፈልጋቸውን በግንባር በመገኘት እየረዱ ላሉ ትርፍ አልባ ድርጅቶች ድጎማ መጨመር ነው። የትርፍ አልባ አቅራቢዎቻችን፣ የካውንቲውን አስደናቂ ብዝሓነት ሲያንጸባርቁ፣ ከታላላቅ ሃብቶቻችን አንዱ ናቸው። ፍላጎቶችም እየጨመሩ ሲመጡ እና ስፋት ያለው የህብረተሰብ ውጥረቶች የፌዴራል መንግስቱን ድጋፍ ስጋት ላይ በሚጥሉበት ሰዓት፣ ስራቸው በጣም አስፈላጊ ነው። በጉያችን እየጨመረ የመጣውን ድህነት በጠራ አመለካከት እና በቁርጠኝነት መጋፈጥ አለብን፤ በጀታችንም ይህንን ያደርጋል። ለጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች የትርፍ አልባ አቅራቢዎች የ 2 በመቶ ጭማሪ ስናቀርብ የዘወትር ቤት አልባነትን ለማጥፋት የሚሰሩትን፣ የርሃብ አደጋን የሚመከቱ፣ በጅጉ ለተጋለጡትም አስፈላጊውን የህክምና አገልግሎቶች የሚያቀርቡትን፣ እናም በማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን የአእምሮ ጤና ችግሮችን ለሚጋፈጡት ትርፍ አልባዎቻችን የካውንስሉን ልገሳ ጨምረናል።

እየተለወጠ ስላለው ስነ ህዝባችን አዘውትረን እናወራለን። የሚገባውን ትኩረት ያላገኘው አንዱ ለውጥ ቢኖር በጅጉ ያደገው የአረጋውያን ህዝባችን መጠን ነው። በ 2020፣ 20 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን አረጋውያን ሲሆኑ አረጋውያኖቻችን በካውንቲያችን እንዲቆዩ እንፈልጋለን። ይህ በጀት አረጋውያኖቻችን እና የቤተሰብ አባሎቻቸው ስለእንክብካቤ ፍላጎቶቻቸው እንዴት የተሻሉ ውሳኔዎችን ሊያደርጉ እንደሚችሉ እንዲረዱ፣ የካውንቲውን ለአረጋውያን የምሳ ፕሮግራም ለማስፋፋት፣ እና የአዋቂ ጥበቃ አገልግሎቶችን አቅም በማጠናከር በአረጋውያን ላይ ሪፓርት የተደረጉ ማጭበርበሮችን ወይም ጥቃቶችን አጣርቶ ለማወቅ ይረዳል። እንዲሁም የአረጋውያን ቁጥር አንድ የመጓጓዣ ጥያቄ የሆነውን የአረጋውያን ነጻ መጓጓዣ በቅዳሜዎች በማሳደግ ግባችንን መተናል።

በተጨማሪም የጠነከረ የንግድ ሁኔታ እንዲፈጠር እርምጃዎችን ወስደናል። ትናንሽ ንግድ ተቋማት የካውንቲያችን ኢኮኖሚ የደም ቡዋንብዋ ናቸው። የንግድ መፍትሔዎች ቡድንን በመፍጠር፣ የቁጥጥር መስመሮቻችንን በተሻለ መንገድ ለመጓዝ የበለጠ እድል ይኖራቸዋል። በካውንቲው ሁሉ ጥረት ለሚያደርጉ ስራ ፈጣሪዎች ጥቃቅን ብድሮችን በማቅረብ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መነሻ ካፒታል እናቀርባለን፤ እንዲሁም ብዙ ስራዎችን ወደ ኢስት ካውንቲ ለማምጣት መነሳሳቶችን እንተገብራለን። ለሞንትጎመሪ

ካውንቲ የኢኮኖሚ እድገት ኮርፖሬሽን እና ወርክሶርስ ሞንትጎመሪ የተፈለጉትን ድጎማዎች አቅርበናል፤ እነዚህም በካውንቲያችን ላለው የኢኮኖሚ እድገት እና የስራ ሃይል ስልጠና መምጣት ምክኒያቶች ሆነዋል። እንዲያሳኩት እንፈልጋለን።

ልክ በአገሪቱዋ እንዳለ ማንኛውም ለመኖር የሚመች ቦታ የተመጣጣኝ ክፍያ መኖሪያ ቤት ለካውንቲያችን አዳጋች ችግር መሆኑን ቀጥሎዋል። በዚህም ጉዳይ ላይ በእጥፍ ስንዘምትበት፣ ያለንን አማራጮች ሁሉ እየተጠቀምን ነው፤ ይህም የተመጣጣኝ ክፍያ መኖሪያ ቤቶች ብዛትን ለመጨመር ያወጣነውን ማስተር እቅድ ይጨምራል። ይህ በጀት ባለፉት ሰባት አመታት ውስጥ ከነበረው ሁሉ የበለጠ ድጎማ ለመኖሪያ ቤቶች ተነሳሽነት ድጎማ ሲሰጥ፣ ይህም መጠን በድምሩ $59 ሚሊዮን ነው። በተጨማሪም በካውንስሉ የቅርብ የአከራይ ተከራይ ህግ የወጣውን ለበለጠ የተከራይ ተሙዋጋችነት ድጎማ በማቅረብ ሂደቱን አፋጥነነዋል።

ከመጓጓዣ ጋር የተያያዙ ነገሮች በዝርዝራችን ላይ ከፍ ብለው የተቀመጡ ሲሆን ይህም በካውንቲያችን ባለው የትራፊክ ሁኔታ የተነሳ ነው። የአውቶቡስ አገልግሎትን ቀልጣፋ እና ፈጣን አገልግሎቶችን በማጎልበት ስናጠናክር በተለይም በራውት 29 እና ራውት 355—የካውንቲያችን በጣም ወሳኝ መስመሮችን አጎልብተናል። በተመሳሳይ ወቅት፣ የአውቶቡስ ፈጣን ትራንዚትን ለመተግበር ወሳኝ እርምጃ ወስደናል። ራውት 29 በ $10 ሚሊዮን የፌዴራል ድጎማ በመታገዝ የምንሰራበት የመጀመሪያ ኮሪደር ይሆናል። በክላርክስበርግ እና በአፕካውንቲ አካባቢ ያሉት አዲስ ራይድ ኦን ራውቶች በፍጥነት እያደጉ ካሉት የካውንቲያችን ክፍሎች ለአንዱ የተፈለጉትን አገልግሎቶች ያቀርባሉ። የጉዞ ጊዜያትን ከ 10 እስከ 15 በመቶ በመቀነስ ተጓዙን ህብረተሰብ የሚረዳውን ልዩ የሆነውን የትራፊክ ምልክት መስጫውን ለመተግበር ወደፊት እየተራመድን ነው።

የመንገዶቻችንን ሁኔታም ግንዛቤያችን ውስጥ አለ። አብዛኛዎቹ ያሉበት ሁኔታ ማህበረሰባችን በሚጠብቀው ወይም በሚገባው ሁኔታ ላይ አይደሉም። ያንንም ችግር ለመቅረፍ ተዘጋጅተናል ተጨማሪ $6.8 ሚሊዮን በማቅረብ ለሚቀጥለው አመት በጠቅላላ $11.9 ሚሊዮን ከመሰረታዊ ሃላፊነቶቻችን አንዱን ለማሙዋላት ለሚደረገው መሻሻል እናውላለን።

ይህንን ሁሉ ያደረግነው የካውንቲ መንግስት ከሚያቀባቸው መሰረታዊ ከሆኑ አገልግሎቶች ጎን ለጎን ሲሆን እነዚህም፥

- የህዝብ ደህንነት በጀታችንን በመጨመር የምሽት ፓሊስ ዲፓርትመንት በድጋሚ በመመለስ እና 16 አዳዲስ የጥበቃ ኦፊሰሮቻንን እና ሁለት የማህበረሰብ ተሳትፎ ኦፊሰሮችን በመጨመር ነው።

- በሶስት ቅርንጫፎች የመጽሃፍት ቤት ሰዓታትን በማራዘም እና መጽሃፍት ቤቶቻችን እና የመዝናኛ ቦታዎቻችን ንጹህ እና የሚስቡ የህዝብ ቦታዎች ሆነው እንዲቆዩ ድጎማ ጨምረናል።

በመጨረሻም፣ ከሌሎች ማህበረሰቦች ካውንቲያችንን ለየት ባለ ደረጃ የሚያስቀምጠን ብዬ ከማስባቸው እሴቶች አንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነፍስ ብዬ ስለምጠራው ነገር ያለን ቁርጠኝነት ነው። ነፍሳችንን የሚመግበውን ስነ ጥበብ ዋጋ እንሰጣለን፤ እንዲሁም የሚያረጋጋንን ተፈጥሮ ዋጋ እንሰጣለን። ይህ በጀት እነዚህን እሴቶችም ያንጸባርቃል። ለታላላቆቹ የስነ ጥበባት ድርጅቶች፣ ብሄራዊ ፊልሃርሞኒክን ጨምሮ፣ ድጎማዎችን ጨምረናል። ለፓርኮች ዲፓርትመንትም ያለንን ድጎማ መልሰን ስናድስ ይህም በተደጋጋሚ የካውንቲያችን በጣም ዋጋ ካላቸው ሃብቶች ውስጥ የሆኑትን ታላላቅ ፓርኮቻችን መንከባከብ እንዲቀጥሉ ያስችላቸዋል። ይህ ድጎማ የመጫወቻ ሜዳዎቻችንን፣ አለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ትሬይል ስርኣት ያድሳል፤ እንዲሁም በጣም ስራ ላይ የዋሉትን ፓርኮች ለማደስ እና ፕሮግራም ለማድረግ ያግዛል። ነዋሪዎቻችን ለዛፎች ዋጋ ይሰጣሉ እናም በካውንቲያችን ላሉ አካባቢዎች ላይ ዛፍ ለመትከል ወደ ግማሽ ሚሊዮን ዶላሮች የሚጠጋ ጨምረናል።

የበጀት ሂደት አድካሚ ስራ ሲሆን ብዙ ጊዜ ከባድ ውሳኔዎችን ይጠይቃል። እኛን ለማገዝ የምሽት ሰአታትን እና የሳምንት ማብቂያዎችን የሰሩ፣ ያለ ወሳኝ የካውንስላችን ሰራተኞች ድጋፍ፣ ይህ ሂደት ሊሰምር አይችልም ነበር። ለስቲቭ ፋርበር፣ ዶክተር ኦርሊን እና የአምስተኛ ፎቅ ጠቅላላ ሰራተኞች ለአመርቂው ስራችሑ ምስጋና አቀርባለሁ።

እናም እያንዳንዳችን እነዚህን ውሳኔዎች ለማድረግ የሚያስፈልገንን መረጃ እና ድጋፍ እንዳለን ለማረጋገጥ የራሳችን ሰራተኞች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ እናውቃለን። ሁሉንም የቡድኔ አባላት ለብርቱ ስራዎቻቸው ማመስገን እፈልጋለሁ፣ በተለይም ለ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ሲንዲ ጊብሰን፣ ጥልቅ መረዳትዋ እና ባለሙያነትዋ ሁላችንንም ጠቅሞናል።

ነገር ግን ከሁሉም በላይ፣ የምክር ቤት ባልደረቦቼን ማመስገን እፈልጋለሁ። እያንዳንዳችሑ በዚህ በጀት የነዋሪዎቻችን የኑሮ ጥራት እንዲሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጋችሑዋል። የጠቀስኩት እያንዳንዱ ጉዳይ በናንተ ተነሳሽነት የተገኘ ነው። በዚህም የተነሳ፣ የፈጠርነው በጀት ፈዝካሊ ሃላፊነት ያለው፣ እሴቶቻችንን የሚያንጸባርቅ እና ቁልፍ የሆኑትን የመንግስት አገልግሎቶች የሚያጠናክር እናም በጥቅሉ ካውንቲያችን ልዩ የመኖሪያ ቦታ እንዲሆን የሚያደርግ ሆንዋል።

# # # #